የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፫
አዲስ አበባ ሕዳር ፲፭ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

24th Year No.3
ADDIS ABABA 24th November, 2017

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፶፭/፪ሺ፲ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በጂቡቲ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በመንገደኞች ትራንስፖርት አገልገሎት የተደረገዉን ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ ………ገጽ ፱ሺ፱፻፶፮

## Content

Proclamation No.1055/2017

Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Djibouti on Passenger Road Transport Service Ratification Proclamation ……………………..………….. -- Page 9956

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፶፭/ ፪ሺ፲ ዓ.ም

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በጂቡቲ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በመንገደኞች ትራንስፖርት አገልግሎት የተደረገዉን ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በጂቡቲ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በመንገደኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ስምምነት ጥር ፴ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም በጂቡቲ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ጥቅምት ፳፫ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሰት አንቀጽ ፶፭ /፩/ እና /፲፪/ መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

#### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ ‹‹በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በጂቡቲ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በመንገደኞች ትራንስፖርት አገልገሎት የተደረገዉን ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፶፭/፪ሺ፲›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### PROCLAMATION NO. 1055/2017

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE REPUBLIC OF DJIBOUTI ON PASSENGER ROAD TRANSPORT SERVICES**

WHEREAS, the Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Djibouti on Passenger Road Transport Service was signed on February 07, 2015;

**WHEREAS,** the House of peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 2nd day of November, 2017;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

#### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Djibouti on Passenger Road Transport Service Ratification Proclamation No.1055/2017''.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፪. ስምምነቱ ስለመፅደቁ

፩/ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በጂቡቲ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል ጥር ፴ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም በመንገደኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፍ ለመተባበር የተደረገዉ ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

፪/ በስምምነቱ አንቀፅ 3(1) የተመለከተው ብሔራዊ ቋንቋ የሚለው አገላለፅ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በህገ መንግስቱ በተመለከተው መሠረት የፌደራል የሥራ ቋንቋ በሚል ይረዳዋል

## ፫. አስፈፃሚ አካል

ይህን ስምምነት እንዲያስፈፅም የትራንስፖርት ሚኒስቴር በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሕዳር ፲፭ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም**

**ሙላቱ ተሾመ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 2. Ratification of the Agreement

1/ The Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Djibouti on Passenger Road Transport Service, signed on February 07, 2015, is hereby ratified.

2/ According to the constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia we understand as working language the one which expressed as National language in Article 3(1) of the agreement.

## 3. Implementing Organs

The Ministry of Transport is hereby empowered to undertake all acts necessary for the implementation of the Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall come into force up on publication in the Federal Negarit Gazettee.

**Done at Addis Ababa, this 24th day of November, 2017**

**MULATU TESHOME (Dr.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**